# የታላቁ ህዳሴ ግድብ ቦንድ ማብራሪያ ሰነድ

# THE GRAND RENNAISSANCE DAM BOND GUIDELINES

**ቦንዱን በመግዛት በታላቁ የኢትዮጵያ የህዳሴ ግድብ ግንባታ አሻራዎን ያኑሩ!**

**PURCHASE THE BOND AND PUT YOUR FINGER PRINT IN THE CONSTRUCTION OF THE GRAND ETHIOPIAN RENAISSANCE DAM ON THE ABAY RIVER!**


**የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ**<br>
**ሐምሌ 2003**<br>
**<u>አዲስ አበባ</u>**

**ማውጫ**

**ገፅ**


1. መግቢያ........................................................................................... 1
2. የቦንድ ምንነት ........................................................................... 1
3. የህዳሴ ግድብ ቦንድ ጠቀሜታዎች....................................................... 1

**ክፍል አንድ ፡ ታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ቦንድ /በብር ለሽያጭ የቀረበ/**

1. የህዳሴ ግድብ ቦንድ ባህሪያት ..................................................................... 5
2. ቦንድ የሚሸጠው ለማን ነው? ቅድመ ሁኔታዎች ............................................. 6
3. ቦንዱን ለመግዛት መሟላት የሚገባቸው ሁኔታዎች.................................... 6
4. የህዳሴ ቦንድ የመጀጫ ቦታ ..................................................................... 6
5. የህዳሴ ቦንድ የባለቤትነት ወይም ግዢ ማረጋገጫ....................................... 7
6. የህዳሴ ቦንድ ለመግዛት የሚወስደው ጊዜ ........................................................ 7
7. በውጭ አገር ለሚኖሩ የህዳቤ ቦንድን ለመግዛት አማራጭ መንገዶች.................... 7-11
8. በውጭ አገር ለሚኖሩት የገንዘብ መላኪያ አሸፋፈን ............................................ 12
9. የመላኪያ ገንዘብ አሸፋፈን ....................................................................... 12
10. ህዳሴ ቦንድ በሁለተኛ ወገን ስም ስለመግዛት.................................... .................. 12
11. የህዳሴ ቦንድን ለሁለተኛ ወገን ስለማስተላለፍ ...................................................... 13
12. የህዳሴ ቦንድን ወለድና የዋና ገንዘብ (Principal) የክፍያ ሁኔታ................................ 13
13. የህዳሴ ቦንድ ወለድ ክንውንን የተሳካ እና የተቀላጠፈ ለማድረግ የተዘረጋ አሰራር.... 14
14. ከክፍያ ጊዜ በፊት ስለሚመለሱ ቦንዶች ................................................................ 14
15. የተገዛ ቦንድ ቢጠፋ ወይም ቢበላሽ ......................................................................... 14

**<u>ክፍል ሁለት</u>፡ ታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ቦንድ /በውጭ ሀገር ገንዘቦች ለሽያጭ የቀረበ/**

1. የህዳሴ ቦንድ ባህሪያት.............................................................................. 16
2. የቦንዱ ዋጋ ............................................................................................ 16
3. የቦንዱ የክፍያ ጊዜ /Maturity/ ........................................................................ 17
4. የቦንዱ ወለድ.................................... ................................................................ 17
5. ቦንድ ለመግዛት መሟላት የሚገባቸው ሁኔታዎች.................................................. 17
6. ቦንዱን ለመግዛት አማራጭ መንገዶች......................................................................... 17-22
7. የመላኪያ ገንዘብ አሸፋፈን ......................................................................... 22-23
8. የህዳሴ ቦንድን ለሁለተኛ ወገን ስለማስተላለፍ............................................................ 23
9. የህዳሴ ቦንድን በሁለተኛ ወገን ስም ስለመግዛት........................................................ 23
10. የህዳሴ ቦንድ የሽያጭ ክንውን የተሳካ እና የተቀላጠፈ ለማድረግ የተዘረጋ አሰራር...... 23
11. የህዳሴ ቦንድ የዋና ገንዘብ (Principal) የክፍያ ሁኔታ................................................ 23-24
12. በተለየ ሁኔታ የሚስተናገዱ ገጠመኞች ................................................................ 24
13. Annex: Banks that have maintalned SWIFT Bllateral Key with CBE…………… 25-39

## 1. መግቢያ

የኢትዮጵያ መንግሥት በአባይ ወንዝ ላይ ታላቁን የህዳሴ ግድብ ለመገንባት በቁርጠኝነት ተነሳስቷል። ይህን ግንባታ ለማከናወን የሚያስፈልገው የፋይናንስ መጠን ከፍተኛ ሲሆን ይሄንኑ ገንዘብም ሙሉ በሙሉ ከሀገሪቱ ተወላጆች ለማሰባሰብ ታቅዷል፡፡ በመሆኑም የሚፈለገውን ገንዘብ በቁጠባ መልክ ለማሰባሰብ እንዲቻል የህዳሴ ግድብ ቦንድ ለሽያጭ ቀርቧል፡፡ የህዳሴ ግድብ ቦንድ በብር እና በሦስት ዋና ዋና የውጭ ገንዘቦች ማለትም በUSD, Euro እና በPound Sterling የተዘጋጀ ነው፡፡ በቦንድ ግዢ ላይ ተሳታፊ የሚሆኑት በሀገር ውስጥ ያሉ መላ ኢትዮጵያዊያን፤ በውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን እና ትውልደ ኢትዮጵያውያን ሲሆኑ ከቦንድ ግዢ ከሚያገኙት የወለድ ጠቀሜታ በተጨማሪ በታሪካዊው የህዳሴ ግድብ ግንባታ የራሳቸውን አሻራ እንዲያስቀምጡ ዕድል ይፈጥርላቸዋል፡፡

## 2. የቦንድ ምንነት

**ቦንድ** እንደ ፕሮሚሰሪ ኖት ወይም የግምጃ ቤት ሰነድ የብድር (የዕዳ) ሰነድ ነው፡፡ ከሌሎች የአጭር ጊዜ የብድር መንገዶችና ከግምጃ ቤት ሰነድ የሚለየው ለረጅም ጊዜ የሚያገለግል በመሆኑ ብቻ ነው፡፡ ከዚህ ውጪ ቦንድ ልክ እንደ ግምጃ ቤት ሰነድና እንደ ሌሎቹ የአጭር ጊዜ የክፍያ መሳሪያዎች ሁሉ በሁለተኛ ገበያ ለሌላ ሶስተኛ ወገን ሊተላለፍ የሚችል፤ ተመልሶ ሊከፈል የሚችል፤ ወለድ ሊገኝበትና በአካልም ሆነ በኤሌክትሮኒክስ መሳሪያ አማካኝነት የሚሸጥ ነው፡፡

## 3. የህዳሴ ግድብ ቦንድ ጠቀሜታዎች

### 3.1. ለአገር ያለው ጠቀሜታ፡-

- ቁጠባን በማበረታታት እና ለኢንቨስትመንት በማዋል ለአገሪቱ ልማት መፋጠን ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያደርጋል፣
- ውጭ አገር የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን ካላቸው ገቢ በመቆጠብ ለሀገራቸው ልማት የሚያስፈለገውን የውጭ ምንዛሪ ግኝትን በማሳደግ ለራሳቸው ተጠቅመው አገራቸውን እንዲጠቅሙ ያስችላቸዋል፣
- ኢንቨስትመንትን በማስፋፋት ተጨማሪ የሥራ ዕድል ይፈጥራል፣
- የገንዘብና ፋይናንስ ገበያ እንዲስፋፋ ይረዳል፡፡

### 3.2. ለገዢዎች ያለው ጠቀሜታ፡-

- ቦንድ ገዥው ከገቢው በየጊዜው ገንዘብ እንዲቆጥብ በማድረግ ሀብት እንዲፈጥር ያደርገዋል፣
- የመንግስት ዋስትና ያለው በመሆኑ አስተማማኝ ሰነድ ነው፣
- ከቦንድ ግዢ የሚገኘው የወለድ ገቢ ከቀረጥ ነፃ ነው፣
- ቦንዱን ለገዢው ሕጋዊ ወራሾች እንዲሁም ለሌላ ሁለተኛ ወገን በውርስና በስጦታ ማስተላለፍ ይቻላል፣
- ቦንዱን በሁለተኛ ገበያ (secondary market) ለሌላ ሰው ወይንም ድርጅት መሸጥ ይቻላል፣
- እንዲሁም ቦንዱን በዋስትና አሲይዞ ከሀገር ውስጥ ባንክ ገንዘብ መበደር ይቻላል፡፡

4. ይህ የቦንድ ማብራሪያ ሰነድ በሁለት ክፍል የተከፈለ ነው፡፡ ክፍል አንድ በብር ለመሸጥ ታስቦ ስለተዘጋጀው ታላቁ የኢትዮጵያ የህዳሴ ግድብ ቦንድ የሚያብራራ ሲሆን ክፍል ሁለት ደግሞ በውጭ ገንዘቦች ለመሸጥ ስለተዘጋጀው ቦንድ የሚያብራራ ነው፡፡

# ክፍል - አንድ

## ታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ቦንድ

## /በብር ለሽያጭ የቀረበ/

1. **ታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ቦንድ ባህሪያት**

1.1 **የቦንዱ ዓይነት :-**

1.1.1 ወለድ የሚከፈልበት ኩፖን ቦንድ፣
1.1.2 ወለድ የማይከፈለበት ኩፖን ቦንድ፤

1.2 **የቦንዱ ስያሜ :-** ታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ቦንድ፣

1.3 **የቦንዱ ባለቤት:-** የኢትዮጵያ መንግስት (የኢፌዲሪ የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር)፣

1.4 **የቦንዱ አቅራቢ:-** የኢትዮጵያ ልማት ባንክ፣

1.5 **ወኪል ሻጮች:-**

1.5.1 በሀገር ውስጥ፣ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ፣
1.5.2 በውጭ አገር፣ የኢትዮጵያ ኤምባሲዎች/የቆንስላ ጽ/ቤቶች፣
1.5.3 ወደፊት በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገር በኢትዮጵያ ልማት ባንክ የሚወከሉ ሌሎች ድርጅቶች፣

1.6 **ዝቅተኛ እና ከፍተኛ የቦንዱ መሸጫ ዋጋ :-**

1.6.1 በሀገር ውስጥ ብር 50
1.6.2 በውጭ ሀገር ብር 500
1.6.3 ከፍተኛ የግዥ መጠን፣ የጣራ ገደብ የለውም፣

1.7 **ለሽያጭ የቀረቡ የቦንድ ዓይነቶች፣**

1.7.1 ባለ ብር 25
1.7.2 ባለ ብር 50
1.7.3 ባለ ብር 100
1.7.4 ባለ ብር 300
1.7.5 ባለ ብር 500
1.7.6 ባለ ብር 1000
1.7.7 ባለ ብር 3000
1.7.8 ባለ ብር 5000
1.7.9 ባለ ብር 10000
1.7.10 ባለ ብር 50000
1.7.11 ባለ ብር 100000
1.7.12 ባለ ብር 200000
1.7.13 ባለ ብር 500000
1.7.14 ባለ ብር 1000000

1.8 **የቦንዱ የክፍያ ጊዜ:-**

- ከ1-5 ዓመት፣
- ከ5 ዓመት በላይ፣

1.9 **ወለድ ለሚከፈልባቸው ቦንዶች የሚከፈለው የወለድ መጣኔ:-**

1.9.1 ከ1-5 ዓመት የክፍያ ጊዜ ላላቸው 5.5 በመቶ፣
1.9.2 ከ5 ዓመት በላይ የክፍያ ጊዜ ላላቸው ቦንዶች 6 በመቶ፣

1.10 **ወለድ ለሚከፈልባቸው ቦንዶች የወለድ የክፍያ ጊዜ:-**

በየግማሽ ዓመቱ እ.ኤ.አ ጁን 30 እና ዲሴምበር 31 (በኢትዮጵያ አቆጣጠር ሰኔ 22 እና ታህሳስ 22) ላይ ይሆናል፡፡ ይህም ወለድ በየወሩ እየተሰላ ቆይቶ በየስድስት ወሩ ለቦንድ ገዥው ይከፈላል ወይም የቦንድ ገዥው በሀገር ውስጥ የከፈተው የቁጠባ ሂሳብ ካለ በቀጥታ ገቢ ይደረግለታል፡፡

1.11 **ወለድ መታሰብ የሚጀምረው፣** ቦንዱ ከተገዛበት ቀን አንስቶ ነው፣

1.12 **ቦንዱ ዋና /principal/ ገንዘብ የክፍያ ጊዜ:-** በክፍያው ዓመት መጨረሻ /Maturity Date/ ላይ ይሆናል፡፡

## 2. ቦንዱ የሚሸጠው ለማን ነው? ቅድመ ሁኔታዎቹስ?

2.1 ቦንዱን ለመግዛት የተቀመጠ ምንም ኣይነት ቅድመ ሁኔታ የለም፡፡ ማንኛውም ኢትዮጵያዊ/ት እና ትውልደ ኢትዮጵያዊ/ት የሆነ ዕድሜ ሳይለይ በተዘጋጀው የቦንድ የሽያጭ ቅጽ (ፎርም) ላይ የራሱን/ራሷን አጭር መረጃና አድራሻ በማስመዝገብ የሚፈልገውን/የምትፈልገውን ያህል ቦንድ መግዛት ይችላል/ትችላለች፡፡

2.2 ኢትዮጵያ ውስጥ የሚኖር የውጭ አገር ዜጋ የህዳሴ ቦንድ መግዛት ከፈለገ በብር ወይም በውጭ ምንዛሪ መግዛት ይችላል፡፡ ነገር ግን ወለድና ዋናው ገንዘብ ለገዢው የሚከፈለው በሀገር ውስጥ ካለ እና በብር ብቻ ይሆናል፡፡

2.3 ብዙ ሆነው የህዳሴ ቦንድ በጋራ መግዛት ለሚፈልጉ ቦንዱ ላይ "እነ አቶ/ወ/ሮ----------" ተብሎ ይሞላል፡፡ የቦንዱ ገዢዎች ስም ዝርዝርና ፊርማቸው ተጽፎ ከሚሞላው የቦንድ ሽያጭ ቅጽ ጋር መያያዝ አለበት፡፡ ቦንዱ ላይ የሚፈርመውን ሰው መርጠው/እሱም በተያያዘው የስም ዝርዝር ላይ መጠቀስ አለበት/ቦንዱን ሊገዙ ይችላሉ፡፡ በየጊዜው የሚከፈለው ወለድና ዋና ገንዘብ በማን ስም መሆን እንዳለበት ውክልና መስጠት ከፈለጉ ወይንም ሁሉም አንድ ላይ ቀርበው መውሰድ ከፈለጉ በዝርዝሩ ውስጥ መጠቀስ አለበት፡፡

## 3. ቦንዱን ለመግዛት መሟላት የሚገባቸው ሁኔታዎች፣

3.1. አቅመ አዳም/ሔዋን የደረሱ፡- የቀበሌ ወይም የመስሪያ ቤት መታወቂያ
3.2. ለሕፃናት፡- የልደት ካርድ፣
3.3. ለተማሪዎች፡- የትምህርት ቤት ወይም የቀበሌ መታወቂያ፣
3.4. በውጭ ሀገር ለሚኖሩ ኢትዩጵያዊያን፡- የኢትዮጵያ ፓስፖርት፣ ፓስፖርት የሌላቸው የኮሙኒቲ መታወቂያ፣
3.5. ውጭ ሀገር የሚኖሩ ትውልደ ኢትጵያውያን፡- ዜግነት የወሰዱበት ሀገር ፓስፖርት እና የኢትዮጵያዊነት ማረጋገጫ መታወቂያ፣
3.6. በተራ ቁጥር 3.1 እና 3.5 ለተጠቀሱት አንድ ጉርድ ፎቶ ግራፍ (passport size) ማቅረብ አለባቸው፡፡

## 4. የህዳሴ ቦንድ የመሸጫ ቦታ

### 4.1. በሀገር ውስጥ፣

- በኢትዮጵያ ልማት ባንክ ዋና መሥሪያ ቤት፣ በሁሉም ቅርንጫፎቹና ንዑስ ቅርንጫፎቹ፣
- በሁሉም የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ቅርንጫፎች፣
- ወደፊት የኢትዮጵያ ልማት ባንክ በውክልና እንዲሠሩ በሚመርጣቸው ተቋማት፣

### 4.2 በውጭ ሀገር፣

- በኢትዮጵያ ኤምባሲዎች/በቋሚ መልዕክተኛ ጽ/ቤቶች/በቁንጽላ ጽ/ቤቶች፣
- ወደፊት ባንኩ በውጭ ሀገር ቦንዱን እንዲሸጡ በሚወክላቸው ተቋማት፣

## 5. የህዳሴ ቦንድ የባለቤትነት ወይም ግዢ ማረጋገጫ

5.1. ቦንድ ገዥው የገዛውን የህዳሴ ቦንድ መጠን የሚያሳይ ኩፖን ከሽያጭ ቅፁ ዋናው ኮፒ ጋር ይሰጠዋል፣
5.2. ቦንድ ገዥው የገዛውን ቦንድ ኩፖን ሻጩ ዘንድ ማስቀመጥ ቢፈልግ ሻጭ የመረካከቢያ ሰነድ (ሰርቲፊኬት) ፈርሞ ለገዥው በመስጠት ኩፖኑን ያስቀምጥለታል ወይም ወደሚቀመጥበት ቦታ ይልካል፣
5.3. ቦንድ ገዥው በራሱ ፍላጐት ላይ ተመስርቶ ሀገር ውስጥ ባሉት በየትኛውም ባንክ ዘንድ በብር ሂሳብ ከፍቶ በየስድስት ወሩ የሚከፈለው ወለድና ዋናው ገንዘብ ሲመለስለት ገንዘቡ በሂሳቡ ውስጥ እንዲገባለት ባንኩን/ወኪሉን ማዘዝ ይችላል፡፡

## 6. የህዳሴ ቦንድ ለመግዛት የሚወስደው ጊዜ፣

በተራ ቁጥር 2 እና 3 ላይ የተጠቀሰውን መረጃ አሟልቶ የቀረበ ቦንዱን ለመግዛት ከ10-15 ደቂቃ ብቻ ይወስድበታል፣

## 7. በውጭ አገር ለሚኖሩ የህዳሴ ቦንድን ለመግዛት አማራጭ መንገዶች

በውጭ ሀገር የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን/ትውልደ ኢትዮጵያውያን የህዳሴ ቦንዱን ኢትዮጵያ በምትገበያይባቸው የውጭ ምንዛሪ ገንዘቦች መግዛት ይችላሉ፡፡ በካሽ ከሆነ ግን በውጭ ሀገር ገንዘብ ማለትም በUSD ወይም Euro ወይም Poud Sterling/ ወይም በብር መግዛት ይችላሉ፡፡ በየስድስት ወሩ ወለድና ዋናው ገንዘብ ተመላሽ ተደርጐ የሚከፈላቸው ግን በብር ነው፡፡ ቦንዱ በብር ሲገዛ በዕለቱ በዋለው የውጭ ምንዛሪ ተመን /Exchange Rate/ ተሰልቶ ይሆናል፡፡

### 7.1. የክፍያውን ገንዘብ በስዊፍት /SWIFT/ ወደ ኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ማስተላለፍ

#### 7.1.1 በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ correspondent banks በኩል

የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የSWIFT ግንኙነት ካላቸው 40 ታላላቅ ባንኮች ጋር (ሠንጠረዥ 1 ይመልከቱ) የ correspondent banking ግንኙነት አለው፡፡ እነዚህ ባንኮች በብዙ ሀገራት ቅንጫፎች ያሏቸው በመሆኑ ማንኛውም ቦንድ ለመግዛት የሚፈልግ ሰው ወደ እነዚህ ቅንጫፎች በመሄድ በቀላሉ ገንዘቡን ማስተላለፍ ይችላል፡፡

ክፍያውን ለማከናወን የሚከተሉትን ቅደም ተከተሎች (steps) በመከተል በቀላሉ መፈፀም ይቻላል፡፡

Step 1:- ገዢው በቅድሚያ ወደ አቅራቢያው ባንክ በመሄድ ገንዘቡን በSWIFT በሚከተለው አድራሻ መላክ ይጠበቅበታል፡፡

**የዶላር አካውንት አድራሻ**

```
Commercial Bank of Ethiopia, Churchil Avenue
International Banking Trade Service
Foreign Transfer NR/NT Accounts
Account No. 0270217976800
SWIFT Code:  CBETETA
```

**የዩሮ አካውንት አድራሻ**

```
Commercial Bank of Ethiopia, Churchil Avenue
Trade Service
Foreign Transfer NR/NT Accounts
Account No.
SWIFT Code:  CBETETA
```

**የፓውንድ ስተርሊንግ አካውንት አድራሻ**

Commercial Bank of Ethiopia, Churchil Avenue
Trade Service
Foreign Transfer NR/NT Accounts
Account No.
SWIFT Code: CBETETA

Step 2:- ገገርው ገንዘቡን የላከበትን ደረሰኝ ኮፒ ከፓስፖርት ኮፒ ወይም የኮሚዩኒቲ መታወቂያ ወይም የተወላጅነት ማረጋገጫ መታወቂያ ኮፒ ጋር አያይዞ ከሚከተሉት አማራጮች ውስጥ በመጠቀም ለኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ይልካል፡፡

1. በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የe-mail አድራሻ (hidasebond@combanketh.com)

2. በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የፖስታ አድራሻ
   ለኢትዮጵያ ንግድ ባንክ
   ፖ.ሣ.ቁ ፡ 255
   አዲስ አበባ
3. አቅራቢያው በሚገኝ ኤምባሲ ወይም ቆንሲላ ወይም ልዩ መልዕክተኛ ጽ/ቤት
4. በግለሰብ በኩል

Step 3:- የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ መረጃው እንደደረሰው ገንዘቡ በትክክል ገቢ መደረጉን በማረጋገጥ ገገርው በመረጠው አድራሻ[1] ቦንዱ እንዲደርሰው ያደርጋል፡፡ ገንዘቡ ስለመድረሱም የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ለገገርው በኢሜይል አድራሻው ማረጋገጫ ይልክለታል፡፡

**ሠንጠረዥ ፲፡- የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የኮረስፖንደንት ሂሳብ የከፈተባቸው ባንኮች ዝርዝር ከሚገኙበት ሀገር**

| No. | Name of the Bank | Address |
|---|---|---|
| 1 | African Import Export | Any country where its branch is available |
| 2 | Banca Nationale Del Lavoro SPA | " |
| 3 | Bank of India (Overseas Branch) | " |
| 4 | Banque de Commarce et de Placements | " |
| 5 | Barclays Bank Plc | " |
| 6 | BHF Bank -AKTIENGESELLSCHAFT | " |
| 7 | BNP-Paribas SA | " |
| 8 | Citibank NA | " |
| 9 | Commerz Bank A.G. | " |
| 10 | Credit Agricole - Banque Indosuer Mer Rouge | " |
| 11 | Credit Suisse | " |
| 12 | Danske Bank A/S | " |
| 13 | Deutsche Bank A.G. | " |
| 14 | Deutsche Bank Nederland N.V. (Formerly Hollandsche Bank Unie NV (HBU) | " |
| 15 | Deutche Bank Trust Co, Americas | " |

[1] የገገርው ወይም የህጋዊ ወኪሉ አድራሻ ወይም በአቅራቢያው የሚገኝ ኤምባሲ ሊሆን ይችላል፡፡

| No. | Name of the Bank | Address |
|---|---|---|
| 16 | Dz Bank AG Deutche Zentral- Genossenschattsbank | " |
| 17 | Emporiki Bank of Greece S.A. | " |
| 18 | HSBC Bank Plc | " |
| 19 | ING Belgium SA/NV | " |
| 20 | Intesa Sanpaolo S.P.A | " |
| 21 | JP Morgan Chase Bank NA | " |
| 22 | Kenya Commercial Bank Ltd | " |
| 23 | Liyods TSB Bank Plc | " |
| 24 | Mashrekbank PSC | " |
| 25 | National West Minister Bank Plc | Any country where its branch is available |
| 26 | Natixis | " |
| 27 | Nordea Bank AB (Pub1) | " |
| 28 | Nordea Bank Norge ASA | " |
| 29 | Royal Bank of Canada | " |
| 30 | Saudi Hollandi Bank | " |
| 31 | Skandinaviska Enskilda Banken AB (Pub1) | " |
| 32 | Standard Chartered Bank | " |
| 33 | State Bank of India, International Service Branch (ISB) | " |
| 34 | Svenska Handlesbanken AB (Pub1) | " |
| 35 | The Bank of Tokyo Mitsubishi UFG Ltd | " |
| 36 | The Export- Import Bank of China | " |
| 37 | The Royal Bank of Scotland PLC (RBC) | " |
| 38 | The Standard Bank of South Africa Ltd | " |
| 39 | UBS AG H.O | " |
| 40 | Uni Credito SPA, Milano | " |

### 7.1.2 የcorrespondent ሂሳብ በሌለባቸው ባንኮች (Banks having SWIFT Bilateral Key with CBE) በኩል

የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የ correspondent ሂሳብ ከከፈተባቸው 40 ታላላቅ ባንኮች በተጨማሪ የ correspondent ሂሳብ ካልከፈተባቸው 384 ባንኮች ጋር የ SWIFT ግንኙነት አለው፡፡ እነዚህ ባንኮች በብዙ ሃገራት ቅንጫፎች ያሏቸው በመሆኑ የቦንድ ግዢ ለመፈፀም የሚፈልግ ማንኛውም ግለሰብ ወደ እነዚህ ቅንጫፎች በመቅረብ ክፍያውን በቀላሉ ወደ ኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ማስተላለፍ ይችላል፡፡ የባንኮቹ ዝርዝር ከዚህ ሰነድ ጀርባ አባሪ (Annex) የተደረገ

ሲሆን በተጨማሪም ከየኤምባሲዎቹና የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ድረ-ገፅ (www.combanketh.com) ማግኘት ይቻላል፡፡

ገዥው ክፍያ ለመፈፀም በተ.ቁ. 7 ንዑስ ተ.ቁ. 7.1.1 ሥር የተዘረዘሩት ቅደም ተከተሎች (steps) መከተል ይችላል፡፡

### 7.2. የክፍያውን ገንዘብ በኤምባሲ በኩል ወደ ኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ማስተላለፍ

ማንኛውም ሰው በአቅራቢያው በሚገኝ ኤምባሲ ወይም ቆንሲላ ወይም ልዩ መልዕክተኛ ጽ/ቤት በመቅረብ የቦንድ ግዢ መፈፀም ይችላል፡፡ ኤምባሲ ተሄዶ ለሚፈፀም ማንኛውም የቦንድ ግዢ የመላኪያ ክፍያ አይጠየቅም፡፡

Step 1:- ገዥው ፓስፖርት ወይም የኮሚኒቲ መታወቂያ ወይም የተወላጅነት ማረጋገጫ መታወቂያ ይዞ ወደ ›?Uvc= በመቅረብ የማመልከቻ ቅፅ ይሞላል፡፡

Step 2:- ገዥው ክፍያውን ለኤምባሲ ሲፈጽም የቦንድ ኩፖን ወዲያውኑ ከኤምባሲው ያገኛል፡፡

### 7.3. የክፍያውን ገንዘብ በገንዘብ አስተላላፊ ኤጀንት /Money transfer Agent/ በኩል ወደ ኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ማስተላለፍ

በመካከለኛው ምስራቅና በለንደን የሚገኙ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን ከዚህ በታች በሠንጠረዥ 2 የተዘረዘሩትን የሐዋላ ድርጅቶች በመጠቀም የቦንድ ግዢ መፈፀም የሚችሉ ሲሆን የክፍያውንም ገንዘብ ወደ ኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የሚከተሉትን ቅደም ተከተሎች (steps) በመከተል በቀላሉ ማስተላለፍ ይችላሉ፡፡

Step 1:- ገዢው ፓስፖርት ወይም የመኖሪያ ፈቃድ ይዞ የሐዋላ ድርጅቶቹ ጋር በመቅረብ ገንዘቡን በሚከተለው አድራሻ ወደ ኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ማስተላለፍ ይችላል፡፡ ክፍያውን ለማስተላለፍ የመላኪያ ወጪ ሙሉ በሙሉ በኢትዮጵያ ልማት ባንክ የሚሸፈን ይሆናል፡፡

**የዶላር አካውንት አድራሻ**

Commercial Bank of Ethiopia, Churchil Avenue
Trade Service
Foreign Transfer NR/NT Accounts
Account No. 0270217976800
SWIFT Code: CBETETA

**የዩሮ አካውንት አድራሻ**

Commercial Bank of Ethiopia, Churchil Avenue
Trade Service
Foreign Transfer NR/NT Accounts
Account No.
SWIFT Code: CBETETA

**የፓውንድ ስተርሊንግ አካውንት አድራሻ**

Commercial Bank of Ethiopia, Churchil Avenue
Trade Service
Foreign Transfer NR/NT Accounts
Account No.
SWIFT Code: CBETETA

Step 2:- ገዢው ገንዘቡን ያስተላለፈበትን ደረሰኝ ከፓስፖርት ኮፒ ወይም የመኖሪያ ፈቃድ ኮፒ ጋር አያይዞ ለኤምባሲው ይሰጣል/ ይልካል ወይም ለኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ይልካል፡፡

Step 3:- የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ መረጃው እንደደረሰው ገንዘቡ በትክክል ገቢ መደረጉን በማረጋገጥ ገዢው በመረጠው አድራሻ ቦንዱ እንዲደርሰው ያደርጋል፡፡ ገንዘቡ ስለመድረሱም የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ለገዢው በኢሜይል አድራሻው ማረጋገጫ ይልክለታል፡፡

**ሠንጠረዥ 2፡- የሐዋላ ድርጅቶች ዝርዝር ከነአድራሻቸውና የሚሰሩባቸው ሀገራት**

| ተ.ቁ | የሐዋላ ድርጅቱ ስም | አድራሻ | የሚሰሩባቸው አገሮች |
|---|---|---|---|
| 1. | ላሪ ኤክስቼንጅ | Tel. 97126223225<br>Fax 97126223220<br>P.O.Box 988 Abudhabi, UAE | ዱባይ፣ አቡዳቢ፣ ሱዳን |
| 2. | ስፒድ ረሚት | Tel. +96614774770<br>Fax +966500584993<br>Samba Financial Group,<br>P.O.Box 833, Riyad, 11421 kindgom of Saudi Arabia | ጅዳ፣ ሪያድ እና አካባቢው |
| 3. | ዘንጅ ኤክስቼንጅ | Tel. 97317253171<br>Fax 97317214405 | ባህሬን |
| 4. | አላሙዲ ኤክስቼንጅ | Tel. 6474515<br>Fax 6477733<br>P.O.Box 123Jeddah 21411 | ጅዳ |
| 5. | ብሉ ናይል አፍሪካን አርት | Tel. (442)7956162303<br>Fax 4422076222244<br>300 Clapharm Road<br>London SW99AE<br>London<br>UK | ለንደን |
| 6. | ኤክስፐረስ የሐዋላ አገልግሎት | Tel. 97126521376<br>Fax 97126355890<br>P.O.Box 170 Abudhabi, UAE | ዱባይና ኩዌት |

### 7.4. በኢትዮጵያ ውስጥ በሚገኙ ባንኮች ውስጥ ከሚገኙ የውጭ ምንዛሪ ሒሳብ ብቻ ክፍያውን በብር ወይም በውጭ ምንዛሪ መፈፀም

7.4.1. በውጭ አገር የሚኖሩ ኢትዮጵያዊያንና ትውልደ ኢትዮጵያዊያን ሃገር ውስጥ ከሚከፍቱት የውጭ ምንዛሪ ሒሳብ ላይ ለቦንዱ ግዢ በብር ወይም በውጭ ምንዛሪ መክፈል ይችላሉ፡፡

7.4.2. ቦንድ ግዢው ከውጭ ምንዛሪ ሒሳብ ላይ ተቀናሽ ተደርጎ በውጭ ምንዛሪ ወይም በብር የሚከፈል ከሆነ ገዢው ከሂሳቡ እንዲቀነስ መስማማቱን የሚገልፅ የተፈረመ የክፍያ ትዕዛዝ በደብዳቤ ወይም በቼክ ለኢትዮጵያ ልማት ባንክ ወይም ለኢትዮጵያ ንግድ ባንክ መላክ ይኖርበታል፡፡

7.4.3. ከግለሰቡ የውጭ ምንዛሪ ሂሳብ ክፍያው ከተፈፀመ በኃላ የኢትዮጵያ ልማት ባንክ ቦንዱን በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር በኩል ይልካል፡፡

### 7.5. በአካል ኢትዮጵያ ውስጥ ተገኝቶ ክፍያውን በጥሬ ገንዘብ መፈጸም፣

7.5.1 ቦንድ ገዢው ወይም ወኪሉ ለዚሁ ተግባር ኤርፖርት በተከፈተው የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ቅርንጫፍ በመቅረብ ክፍያ ይፈፅማል፤ ክፍያ እንደተፈፀመም ባንኩ ቦንዱን ለገዢው ወይም ወኪሉ ይሰጣል፡፡

7.5.2 ከኤርፖርት ውጭ በጥሬ ገንዘብ ግዢ መፈፀም ሚፈልጉ ደንበኞች የያዙትን ገንዘብ /ከ3000 ዶላር በላይ ከሆነ/ ለጉምሩክ አሳውቀው declaration በማግኘት ወደ ኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ማንኛውም ቅርንጫፍ ወይም ዓለም አቀፍ ባንኮች ክፍል ወይም የኢትዮጵያ ልማት ባንክ በመቅረብ የቦንዱን ግዢ መፈፀም ይችላሉ፡፡

## 8. በውጭ አገር ለሚኖሩት የገንዘብ መላኪያ አሸፋፈን

8.1. የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ሂሳብ በከፈተባቸው 40 correspondent banks /ዝርዝራቸው በሠንጠረዥ1 የተገለፀው/ በኩል SWIFT ተጠቅመው በብር 10,000.00 እና በላይ የህዳሴ ቦንድ የገዛ ግለሰብ የመላኪያ ወጪው ሙሉ በሙሉ በኢትዮጵያ ልማት ባንክ የሚሸፈን ይሆናል፡፡

8.2. የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ሂሳብ ባልከፈተባቸው ነገር ግን የ SWIFT ግንኙነት ባላቸው ባንኮች /Bilateral Banks ዝርዝራቸው ከዚህ ማብራሪያ ጀርባ አባሪ ተደርጓል/ በመጠቀም በብር 20,000.00 እና በላይ የህዳሴ ቦንድ የገዛ ግለሰብ የመላኪያ ወጪ ሙሉ በሙሉ በኢትዮጵያ ልማት ባንክ የሚሸፈን ይሆናል፡፡

8.3. የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ሂሳብ የከፈተባቸውን correspondent banks ሳይጠቀም ከብር 10,000.00 በታች ወይም የ SWIFT ግንኙነት ባላቸው ባንኮች ሳይጠቀም ከብር 20,000 በታች የህዳሴ ቦንድ ለመግዛት የሚፈልግ ግለሰብ የመላኪያ ወጪውን በራሱ ይሸፍናል/ትሸፍናለች ወይም በኤምባሲ በኩል በመጠቀም ክፍያ መፈጸም ይችላል/ትችላለች፣

## 9. የመላኪያ ገንዘብ አሸፋፈን

ከላይ በተ.ቁ. 7.1 እና 7.3 መሠረት የቦንድ ግዢ ተፈፅሞ የመላኪያ ወጪ በመንግስት ለሚሸፈንላቸው የመላኪያው ወጪ በሚከተሉት አማራጮች ይፈፀማል፡፡

**አማራጭ 1፡** <u>**የመላኪያ ወጪ ከቦንዱ ዋጋ ላይ ታሳቢ የተደረገ ከሆነ፡**</u>

በዚህ አማራጭ ባንኩ ወይም የሐዋላ ድርጅቱ የመላኪያ ወጪውን ከቦንድ መግዣ ላይ ቀንሶ የሚልክ ስለሆነ የቦንድ ዋጋው የተቀነሰው ተጨምሮለት ይሆናል፡፡

**ለምሳሌ፡-** አንድ ግለሰብ ከብር 1000 ጋር ተመጣጣኝ የሆነ የውጭ ምንዛሪ ዋጋ ያለው የህዳሴ ቦንድ ቢገዛና ከብር 100 ጋር እኩል የሆነ የውጭ ምንዛሪ የመላኪያ ወጪ ከ ብር 1000 ጋር ተመጣጣኝ ከሆነው ላይ ታሳቢ/ተቀራጭ እንዲደረግ ቢፈቅድ ወደ ኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የሚተላለፈው የገንዘብ መጠን ከብር 900 ጋር እኩል የሆነ የውጭ ምንዛሪ ይሆናል፡፡ ነገር ግን ለግለሰቡ የሚላክለት ቦንድ የባለ ብር 1000 ዋጋ ያለው ነው፡፡ ይህም ማለት ከብር 100 ጋር እኩል የሆነ የውጭ ምንዛሪ የመላኪያ ዋጋ ተሸፍኖለታል ማለት ነው፡፡

**አማራጭ 2፡** <u>**የመላኪያ ወጪ በቦንድ ገዢ የተሸፈነ ከሆነ**</u>

በዚህ አማራጭ ቦንድ ገዢው የመላኪያ ወጪውን በተጨማሪነት የከፈለ እንደሆነ ለመላኪያ ያወጣው ገንዘብ ሌላ ተጨማሪ ቦንድ እንደገዛ ተቆጥሮ ይታሰብለታል፡፡

**ለምሳሌ፡-** ግለሰቡ ከብር 1000 ጋር ተመጣጣኝ በሆነ የውጭ ምንዛሪ ዋጋ ያለው የህዳሴ ቦንድ ቢገዛና ከብር 100 ጋር እኩል የሆነ የውጭ ምንዛሪ የመላኪያ ወጪም በተጨማሪነት ቢከፍል በአጠቃላይ የብር 1100 ቦንድ እንደገዛ ይቆጠርለታል (ይሰጠዋል) ማለት ነው፡፡

## 10. ህዳሴ ቦንድ በሁለተኛ ወገን ስም ስለመግዛት

10.1. የህዳሴ ቦንድን ለሌላ ሰው መግዛት ይቻላል፡፡ ነገር ግን ቦንዱ ላይ ስሙ የሚጻፈው ቦንዱ የሚገዛለት/የቦንድ ባለቤት/ ሰው ስም መሆን አለበት፡፡ በሌላ ሰው ስም ቦንዱን የሚገዛው ሰው በቦንዱ ላይ "ስለ" ብሎ መፈረም ይችላል፡፡ በየጊዜው የወለድ ክፍያ የሚፈጸመውና ዋናው ገንዘብ ተመላሽ የሚደረገው ግን ቦንዱ ለተገዛለት ሰው ወይም እሱ/እሷ ሕጋዊ ውክልና ለሰጠው/ችው ሰው ብቻ ይሆናል፡፡

10.2 ውጪ አገር የሚኖሩ ኢትዮጵያዊያን/ትውልደ ኢትዮጵያዊያን በራሳቸው ወይም በወኪላቸው በኩል ከብር 50,000 በላይ የሆነ ቦንድ በሀገር ውስጥ ተገኝተው ለመግዛት የሚፈልጉ ከሆነ፡-

- ገዢው ወይም ወኪሉ ለዚሁ ተግባር ኤርፖርት በተከፈተው የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ቅርንጫፍ በመቅረብ ክፍያ ይፈፅማል ክፍያው እንደተፈፀመም ባንኩ ቦንዱን ለገዢው ወይም ወኪሉ ወዲያውኑ ይሰጣል፡፡
- ከኤርፖርት ውጪ በጥሬ ገንዘብ የቦንድ ግዢ ለመፈፀም የሚፈልጉ ደንበኞች የያዙት ገንዘብ ከዶላር 3000 በላይ ከሆነ ለጉምሩክ አሳውቀው declaration በማግኘት ከኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ዓለም ዓቀፍ ባንኮች ክፍል

በመቅረብ የቦንድ ግዢ መፈፀም ይችላሉ፡፡

10.3 ለአቅመ አዳም/ሔዋን ላልደረሱ ልጆች በወላጆቻቸው(አባት፤ እናት ወይም አሳዳጊ) አማካይነት በቦንዱ ላይ የልጁን/ልጅቷን ስም በመጻፍና "ስለ" ብለው በመፈረም ቦንዱን መግዛት የሚችሉ ሲሆን፣ ልጁ/ልጅቷ 18 ዓመት እስከሚሞላው/ላት ድረስ ከቦንዱ የሚገኘው ጥቅም እንዲቀመጥ ወላጁ /አሳዳጊው ከፈለገ በዚሁ መሠረት ማስተናገድ ይቻላል፡፡

## 11. የህዳሴ ቦንድን ለሁለተኛ ወገን ስለማስተላለፍ

11.1. ቦንድ ገዥው ቦንዱን ለሁለተኛ ወገን በጀርባው ላይ በመፈረም ብቻ በውርስና በስጦታ ለሌላ ሰው ማስተላለፍ፤ ቦንዱን አስይዞ ከሀገር ውስጥ ባንክ ገንዘብ መበደር ወይንም ቦንዱን በሁለተኛ ገበያ /Secondary Market/ ለሌላ ገዢ መሸጥ ይችላል፡፡

11.2 በእያንዳንዱ የቦንድ ኩፖን ጀርባ ላይ ቦንዱን እስከ ሶስት ሰው ድረስ ለማስተላለፍ የሚያስችል ቦታ እንዲኖር የተደረገ ቢሆንም፤ ቦንዱን ከሶስት ሰው በላይ ማስተላለፍ ቢፈለግ በማንኛውም የቦንድ ሽያጭ ጣቢያ/ኤምባሲ/ቆንጽላ ጽ/ቤት ጋር አስተላላፊውና የሚተላለፍለት ሰው በመሄድ እና የቦንድ ማስተላለፊያ ቅጽ/ፎርም/ ላይ አስፈላጊውን መረጃ በመሙላት ማስተላለፍ ይቻላል፡፡

11.3 ቦንዱ ለሌላ ወገን ሲተላለፍ የተላለፈለት ሰው ሲፈልግ /ሀገር ውስጥ ከሆነ/ የቁጠባ ሂሳብ ሊከፈትለት ይችላል፡፡ የሽያጭ ቅጹም በተላለፈለት ሰው ስም ይሰራለታል፡፡

## 12. የህዳሴ ቦንድ ወለድና የዋና ገንዘብ (Principal) የክፍያ ሁኔታ

12.1. ማንኛውም የቦንድ ገዥ በየስድስት ወሩ የሚከፈለውን ወለድና ዋናው ገንዘብ ሲመለስለት ክፍያውን ቦንዱን ከገዛበት ቦታ ያገኛል፣

12.2. ሆኖም የህዳሴ ቦንድን የገዛ ሰው በሥራ ወይም በሌላ ምክንያት ቦንዱን ከገዛበት ስፍራ ቢዛወር በየስድስት ወሩ የሚከፈለውን ወለድ ወይንም ዋናውን ገንዘብ ለማግኘት ከማንኛውም የኢትዮጵያ ልማት ባንክ ወይም የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ቅርንጫፎች በሙሉ ኦርጅናሉን የቦንድ ኩፖን እና የሽያጭ ፎርም ሲያቀርብ ክፍያውን እንዲያገኝ ይመቻችለታል፡፡

12.3. በቁጥር 12.2 የተጠቀሰውን ተግባራዊ ለማድረግ ከፋዩ ባንክ ክፍያውን ከመፈጸሙ በፊት ከሚመለከተው ቦንዱን ከሸጠው ቅርንጫፍ አካል ወኪል ጉዳዩን አሳውቆ በመክፈል መረጃውን ለመጀመሪያ የቦንዱ ሻጭ አካልና ለኢትዮጵያ ልማት ባንክ ዋና መ/ቤት ወዲያውኑ ማድረስ አለበት፡፡

12.4. የህዳሴ ቦንድ የገዛ ሰው በየስድስት ወሩ የሚያገኘውን ወለድ እና የቦንዱ የጊዜ ገደብ ሲጠናቀቅ ዋናውን ተመላሽ ገንዘብ፣

- በብር ሊወስድ፤
- በብር በከፈተው ሂሳብ ገቢ ሊያደርገው፣ ወይም
- ሌላ ቦንድ ሊገዛበት፣ ይችላል፡፡

12.5. አንድ የተሸጠ የህዳሴ ቦንድ የመመለሻው ጊዜ ከደረሰና ቦንዱን የገዛው ግለሰብ ወይም ድርጅት ሳይመጣ ቢቆይ ገንዘቡ በስሙ ተይዞ ከቦንዱ የክፍያ ቀን/Maturity Date/ በኋላ እስከ 10 ዓመት ድረስ ይቆያል፡፡ ነገር ግን ከቦንዱ የመመለሻ ጊዜ በኋላ በቦንዱ ላይ ምንም ወለድ አይታሰብበትም፡፡

12.6. አንድ የተሸጠ ቦንድ የመመለሻ ጊዜው ሲደርስ የአገልግሎት ዘመኑን ማደስ/ማራዘም አይቻልም፡፡ ነገር ግን በቦንዱ ዋጋ ሌላ ቦንድ ሊገዛበት ይችላል፡፡

12.7. አንድ የህዳሴ ቦንድ የገዛ ሰው ለሌላ ሁለተኛ ወገን ሳያስተላልፍ ቢሞት ሕጋዊ ወራሾቹ የውርስ ማስረጃ በማምጣት ከቦንዱ የሚገኘውን ጥቅም ሁሉ ያገኛሉ፡፡

## 13. የህዳሴ ቦንድ ክንውንን የተሳካ እና የተቀላጠፈ ለማድረግ የተዘረጋ አሰራር

የኢትዮጵያ ልማት ባንክ፣ የህዳሴ ቦንድ ሽያጭን እና ግዢን በተመለከተ ዝርዝር የአፈፃጸምና የሂሳብ አያያዝ ማኑዋል አዘጋጅቶ ሥራ ላይ አውሏል፡፡

በዚሁ መሰረት፤

13.1. ሁሉም የህዳሴ ቦንድ የሚሸጡ የኢትዮጵያ ልማት ባንክ እና የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ቅርንጫፎች የህዳሴ ቦንድ ሽያጭ በብር ገቢ የሚሆንበት የህዳሴ ግድብ ቦንድ ሂሳብ እንዲከፍቱ ተደርጓል፤ /ወደፊት ውክልና እንዲሰጣቸው የሚደረጉ አካላት ተመሳሳይ አሥራር ሥራ ላይ ያውላሉ/፡

13.2. በሃገር ውስጥ ከቦንድ ሽያጭ የተሰበሰበው ገንዘብ በየባንኩ ቅርንጫፎች የህዳሴ ግድብ ቦንድ ሂሳብ ውስጥ እንዲገባ ይደረጋል፣

13.3. በውጭ ሀገር እየኖሩ የህዳሴ ቦንድ የሚገዙት የዲያስፖራው አባላት የቦንድ ግዥን ገንዘብ ገቢ የሚያደርጉበት የዶላር አካውንት ሂሳብ ቁጥር፣ የዩሮ አካውንት ሂሳብ ቁጥር እና የፓውንድ ስተርሊንግ አካውንት ሂሳብ ቁጥር በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ፣ ዓለም አቀፍ ባንኮች አገልግሎት/የውጭ ሃዋላ እና NR/NT ክፍል/ ተከፍቷል፡፡

13.4. በእያንዳንዱ የህዳሴ ቦንድ ገዢ ስም የሂሳብ ቋት(Subsidiary Ledger) በሻጩ/ወኪሉ ይያዛል፡፡

13.5. እንደዚሁም ለቁጥጥርና ክትትል ሲባል በኢትዮጵያ ልማት ባንክ ዋና መ/ቤት የእያንዳንዱ የህዳሴ ቦንድ ገዢ ዝርዝር መረጃ (የሂሳብ ቋትን ጨምሮ) ይያዛል፡፡

## 14. ከክፍያ ጊዜ በፊት ስለሚመለሱ ቦንዶች

የህዳሴ ቦንድ ገዢዎች የገዙትን ቦንድ ከክፍያ ጊዜ በፊት ለመመለስ ቢፈልጉ ዕድል
የሚሰጣቸው ሲሆን ዝርዝር አሰራሩ እንደሚከተለው ይሆናል፤

- የክፍያ ጊዜያቸው ከ1-5 ዓመት ለሆኑ የህዳሴ ቦንዶች ገዢው ቦንዱን ከገዛበት ቀን ጀምሮ ቢያንስ 1 ዓመት ጠብቆ ለሻጩ ቦንዱን በመመለስ ገንዘቡን መውሰድ ይችላል፣

- የክፍያ ጊዜያቸው ከ5 ዓመት በላይ ለሆኑ የህዳሴ ቦንዶች ገዢው ቦንዱን ከገዛበት ቀን ጀምሮ ቢያንስ 3 ዓመት ጠብቆ ለሻጩ ቦንዱን በመመለስ ገንዘቡን መውሰድ ይችላል፤

- ከ5 ዓመት በላይ ለሆነ ጊዜ የተገዛ ቦንድ በ5 ዓመት ወይም ከ5 ዓመት በፊት ቢመለስ ወለዱ ከ6 በመቶ ወደ 5.5 በመቶ ተስተካክሎ ይሰላል፡፡

- የገዛውን የህዳሴ ቦንድ ከክፍያ ጊዜው በፊት ተመላሽ የሚያደርግ ደንበኛ ከሚያገኘው ወለድ ላይ መጠነኛ ቅናሽ የሚደረግበት ይሆናል፡፡

## 15. የተገዛ ቦንድ ቢጠፋ ወይም ቢበላሽ፣

15.1 የተገዛ ቦንድ የጠፋበት/የተሰረቀበት ሰው ቦንዱ ለመጥፋቱ/ለመሰረቁ በ24 ሰዓት ውስጥ ለሚመለከተው አካል/ፖሊስ ጽ/ቤት/ ማስመዝገብና መረጃውን መያዝ አለበት፡፡ የመረጃውን ኮፒ ቦንዱ ለመጥፋቱ/ለመሰረቁ ለቦንድ ሻጭ ባንክ ወይም ወኪል በማቅረብ ማስመዝገብ ይጠበቅበታል፡፡

15.2 ኩፖኑ የተሠረቀበት ወይም የጠፋበት ሰው ማስረጃ ይዞ ሻጩ ባንክ ወይም ወኪሉ ዘንድ በመቅረብ በምትኩ ሌላ ማስረጃ ወይም ሠርቲፊኬት መውሰድ ይችላል፡፡

15.3 ኩፖኑ በከፊል ወይንም ሙሉ በሙሉ ቢበላሽ ለባንኩ ወይም ለወኪሉ በማሳወቅ እና የተበላሸውን የቁጠባ ቦንድ ኩፖን በማቅረብ በምትኩ ሌላ ሠርቲፊኬት መውሰድ ይቻላል፡፡


| **<u>አ ድ ራ ሻ</u>** | **<u>Address</u>** |
|---|---|
| የ ኢ ት ዮ ጵ ያ ል ማ ት ባ ን ክ | Development Bank of Ethiopia |
| ዩሴፍ ብሮዝ ቲቶ መንገድ | Josef Broz Tito St. |
| ስልክ 011-551-11-88/89 | Tel.No.011-551-11-88/89 |
| ፋክስ +251-11-551-16-06 | Fax + 251-11-551-16-06 |

# ክፍል ሁለት

## ታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ቦንድ

## /በውጭ ሀገር ገንዘቦች ለሽያጭ የቀረበ/

## 1. የህዳሴ ቦንድ ባህሪያት

1.1 **የቦንዱ ዓይነት** -

- ወለድ የሚከፈልበት ኩፖን ቦንድ
- ወለድ የማይከፈልበት ኩፖን ቦንድ

1.2 **የቦንዱ ስያሜ** - ታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ቦንድ

1.3 **የቦንዱ ባለቤትና አቅራቢ** - የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን

1.4 **የቦንዱ ወኪል ሻጮች** - የኢትዮጳያ ንግድ ባንክ እና ወደፊት የሚወከሉ ሌሎች ድርጅቶች

1.5 **ቦንዱ ለሽያጭ የሚቀርብባቸው ቦታዎች** - በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ፣ ኤምባሲዎች ወይም ቆንስላዎች ወይም ልዩ መልዕክተኛ ጽሕፈት ቤቶች እና ወደፊት የሚገለጹ ሌሎች ወኪሎች

1.6 **ቦንዱ የሚከፈልበት ጊዜ** - የቦንዱ የጊዜ ገደብ ሲያበቃ፡፡

1.7 **የቦንድ ወለድ የሚከፈለው** - በየግማሽ ዓመቱ ፡፡

1.8 **ዋስትና** - መንግሥት ለቦንዱ ሙሉ ዋስትና ሰጥቶታል፡፡

1.9 **የገቢ ግብር** - ከቦንዱ ግዢ የሚገኝ የወለድ ገቢ ከግብር ነፃ ነው፡፡

1.10 **የባንክ ብድር**- ቦንዱን አስይዞ ከሀገር ውስጥ ባንክ ብድር መውሰድ ይቻላል፡፡

## 2. የቦንድ ዋጋ

2.1 ዝቅተኛው የቦንድ ዋጋ (minimum bond value) በዶላር፣ ዩሮ እና ፓውንድ ስተርሊንግ 50 ሆኖ ባለ 100 ፣ 300 ፣ 500 ፣ 1,000 ፣ 3,000 ፣ 5,000 እና 10,000 ቦንዶችም ለገበያ ቀርበዋል፡፡

2.2 በተጨማሪነት ቅንስናሾችን ለማስተናገድ እንዲቻል በዶላር፣ ዩሮ እና ፓውንድ ስተርሊንግ ባለ 5 እና 10 ዋጋ ያላቸው ቦንዶችም ለሽያጭ ቀርበዋል፡፡ ለምሳሌ አንድ ግለሰብ የ55 ዶላር ቦንድ መግዛት ቢፈልግ አንድ ባለ 50 ዶላር ቦንድ እና ተጨማሪ ባለ 5 ዶላር ይሰጠዋል ማለት ነው፡፡

2.3 የቦንዱ ሽያጭ የሚከናወነው በዶላር፣ ፓውንድ ስተርሊንግ፣ ዩሮ፣ ስዊዝ ፍራንክ፣ ሪያል፣ ድርሃም፣ ስዊድሽ እና ኖርዌይ ክሮነር እንዲሁም የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በሚገበያይባቸው ሌሎች የውጭ ሀገር ገንዘቦች ይሆናል።

2.4 ከዶላር፣ ዩሮ እና ፓውንድ ስተርሊንግ ውጪ ሆነው በ2.3 ላይ በተዘረዘሩት የውጭ ገንዘቦች በመጠቀም ግዢ የሚፈፅም ሰው በዕለቱ ባለው የውጭ ምንዛሪ ተቀይሮ ግዢ መፈፀም ይችላል፡፡ የየዕለቱን የምንዛሪ መጣኔ ከኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ድረ-ገፅ መመልከት ይቻላል፡፡

### 3. የቦንድ የክፍያ ጊዜ (maturity)

3.1 የቦንዱ ዝቅተኛ የክፍያ ጊዜ 5 ዓመት ሲሆን ከፍተኛው ደግሞ 10 ዓመት ነው፡፡

### 4. የቦንዱ ወለድ

4.1 ወለድ መታሰብ የሚጀምርበት ጊዜ፡-

የቦንዱ ወለድ መታሰብ የሚጀምረው ቦንዱ ከተገዛበት ወይም የቦንዱ ግዢ ከተፈፀመበት ቀን ጀምሮ ይሆናል፡፡

4.2. የወለድ መጣኔ

የሚከፈለው የወለድ መጣኔ የቦንዱን የክፍያ ጊዜ ያገናዘበ ሆኖ፡-

- 5 ዓመት የክፍያ ጊዜ ላለው---------------LIBOR[2]+1.25 በመቶ
- ከ6-7 ዓመት የክፍያ ጊዜ ላላቸው------- LIBOR+1.5 በመቶ
- ከ8-10 ዓመት የክፍያ ጊዜ ላላቸው-------LIBOR+ 2.0 በመቶ ይሆናል፡፡

4.3. የወለድ አጠቃቀም

- የወለድ ክፍያ የሚፈፀመው የቦንዱ ግዢ የተፈፀመበትን የምንዛሪ ዓይነት መነሻ በማድረግ በዶላር፣ ፓውንድ ስተርሊንግ እና ዩሮ ሲሆን ገዢው ወለዱን፡-
    - በግንባር በመቅረብ ወይም በሕጋዊ ወኪል በኩል መውሰድ፣
    - ለሌላ ተጨማሪ ቦንድ ግዢ ማዋል
    - በውጭ ምንዛሪ ወይም በብር በሚከፍተው ሒሳብ ገቢ ሊያደርግ፣
    - ለተለያዩ ክፍያዎች ሊጠቀምበት ይችላል፡፡

### 5. ቦንድ ለመግዛት መሟላት የሚገባቸው ሁኔታዎች

5.1 ቦንድ የሚሸጠው ለኢትዮጵያዊ ወይም ትውልደ ኢትዮጵያዊ ብቻ ነው፡፡

5.2 ትውልደ ኢትዮጵያ የውጭ ሀገር ዜጐች በተወላጅነት መታወቂያ የቦንድ ግዢ መፈፀም ይችላሉ፡፡

5.3 ፓስፖርት ማቅረብ በማይቻልባቸው አካባቢዎች የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን በአቅራቢያቸው ከሚገኝ ኤምባሲ በተሰጠ የኮሚኒቲ መታወቂያ የቦንድ ግዢ መፈፀም ይችላሉ፡፡

5.4 በመካከለኛው ምስራቅ የሚኖሩ ኢትዮጵያዊያን ፓስፖርታቸው በአሰሪዎች ተይዞ የሚገኝ ከሆነ በአሰሪዎቻቸው አማካኝነት ግዢ መፈፀም ይችላሉ፡፡

5.5 ከውጭ ምንዛሪ ሂሳባቸው ላይ የቦንድ ግዢ መፈፀም የሚፈልጉ ተወላጆች ከሂሳባቸው ወጪ በማድረግ ቦንድ መግዛት ይችላሉ፡፡

### 6. ቦንዱን ለመግዛት አማራጭ መንገዶች

6.1 **የክፍያውን ገንዘብ በስዊፍት /SWIFT/ ወደ ኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ማስተላለፍ**

---

[2] LIBOR፡ London Interbank Offer Rate ማለት በለንደን የገንዘብ ገበያ ባንኮች በየዕለቱ እርስ በእርሳቸው የሚበዳደሩበት የወለድ መጣኔ ነው፡፡ ይህ መጣኔ ብዙ ባንኮች የራሳቸውን የወለድ መጣኔ ለመወሰን እንደመነሻ የሚጠቀሙበት ነው፡፡ የLIBOR መጣኔን በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ድረ-ገፅ ላይ መመልከት ይቻላል፡፡

*6.1.1 በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ correspondent banks በኩል*

የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የSWIFT ግንኙነት ካላቸው 40 ታላላቅ ባንኮች ጋር (**ሠንጠረዥ 1 ይመልከቱ**) የ correspondent banking ግንኙነት አለው፡፡ እነዚህ ባንኮች በብዙ ሀገራት ቅንጫፎች ያሏቸው በመሆኑ ማንኛውም ቦንድ ለመግዛት የሚፈልግ ሰው ወደ እነዚህ ቅንጫፎች በመሄድ በቀላሉ ገንዘቡን ማስተላለፍ ይችላል፡፡

እነዚህን የ Correspondent banks በመጠቀም በዶላር ወይም ዩሮ ወይም ፓውንድ ስተርሊንግ 500 እና በላይ የሆነ የቦንድ ግዢ የሚፈፅም ከሆነ የመላኪያ ገንዘቡ ሙሉ በሙሉ በመንግሥት የሚሸፈን ይሆናል፡፡

ክፍያው ለማከናወን የሚከተሉትን ቅደም ተከተሎች (steps) በመከተል በቀላሉ መፈፀም ይቻላል፡፡

Step 1:- ገዢው በቅድሚያ ወደ አቅራቢያው ባንክ በመሄድ ገንዘቡን በSWIFT በሚከተለው አድራሻ መላክ ይጠበቅበታል፡፡

**የዶላር አካውንት አድራሻ**

Commercial Bank of Ethiopia, Churchil Avenue
Trade Service
Foreign Transfer NR/NT Accounts
Account No. 0270217976800
SWIFT Code: CBETETAA

**የዩሮ አካውንት አድራሻ**

Commercial Bank of Ethiopia, Churchil Avenue
Trade Service
Foreign Transfer NR/NT Accounts
Account No.
SWIFT Code: CBETETAA

**የፓውንድ ስተርሊንግ አካውንት አድራሻ**

Commercial Bank of Ethiopia, Churchil Avenue
Trade Service
Foreign Transfer NR/NT Accounts
Account No.
SWIFT Code: CBETETAA

Step 2:- ገዢው ገንዘቡን የላከበትን ደረሰኝ ኮፒ ከፓስፖርት ኮፒ ወይም የኮሚዩኒቲ መታወቂያ ወይም የተወላጅነት ማረጋገጫ መታወቂያ ኮፒ ጋር አያይዞ ከሚከተሉት አማራጮች ውስጥ በመጠቀም ለኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ይልካል፡፡

1. በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የe-mail አድራሻ (hidasebond@combanketh.com)
2. በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ
   ፖ.ሣ.ቁ ፡ 255
   አዲስ አበባ
3. በአቅራቢያው በሚገኝ ኤምባሲ ወይም ቆንሲላ ወይም ልዩ መልዕክተኛ ጽ/ቤት
4. በግለሰብ በኩል

Step 3፡- የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ መረጃው እንደደረሰው ገንዘቡ በትክክል ገቢ መደረጉን በማረጋገጥ ገዢው በመረጠው አድራሻ[3] ቦንዱ እንዲደርሰው ያደርጋል፡፡ ገንዘቡ ስለመድረሱም የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ለገዢው በኢሜይል አድራሻው ማረጋገጫ ይልክለታል፡፡

[3] የገዢው ወይም የህጋዊ ወኪሉ አድራሻ ወይም በአቅራቢያው የሚገኝ ኤምባሲ ሊሆን ይችላል፡፡

**ሠንጠረዥ ፤- የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የኮረስፖንደንት ሂሳብ የከፈተባቸው ባንኮች ዝርዝር ከነሚገኙበት ሀገር**

| No. | Name of the Bank | Address |
|---|---|---|
| 1 | African Import Export | Any country where the branch is available |
| 2 | Banca Nationale Del Lavoro SPA | " |
| 3 | Bank of India (Overseas Branch) | " |
| 4 | Banque de Commarce et de Placements | " |
| 5 | Barclays Bank Plc | " |
| 6 | BHF Bank -AKTIENGESELLSCHAFT | " |
| 7 | BNP-Paribas SA | " |
| 8 | Citibank NA | " |
| 9 | Commerz Bank A.G. | " |
| 10 | Credit Agricole – Banque Indosuer Mer Rouge | " |
| 11 | Credit Suisse | " |
| 12 | Danske Bank A/S | " |
| 13 | Deutsche Bank A.G. | " |
| 14 | Deutsche Bank Nederland N.V. (Formerly Hollandsche Bank Unie NV (HBU) | " |
| 15 | Deutche Bank Trust Co, Americas | " |
| 16 | Dz Bank AG Deutche Zentral- Genossenschattsbank | " |
| 17 | Emporiki Bank of Greece S.A. | " |
| 18 | HSBC Bank Plc | " |
| 19 | ING Belgium SA/NV | " |
| 20 | Intesa Sanpaolo S.P.A | " |
| 21 | JP Morgan Chase Bank NA | " |
| 22 | Kenya Commercial Bank Ltd | " |
| 23 | Liyods TSB Bank Plc | " |
| 24 | Mashrekbank PSC | " |
| 25 | National West Minister Bank Plc | Any country where the branch is available |

| No. | Name of the Bank | Address |
|---|---|---|
| 26 | Natixis | " |
| 27 | Nordea Bank AB (Pub1) | " |
| 28 | Nordea Bank Norge ASA | " |
| 29 | Royal Bank of Canada | " |
| 30 | Saudi Hollandi Bank | " |
| 31 | Skandinaviska Enskilda Banken AB (Pub1) | " |
| 32 | Standard Chartered Bank | " |
| 33 | State Bank of India, International Service Branch (ISB) | " |
| 34 | Svenska Handlesbanken AB (Pub1) | " |
| 35 | The Bank of Tokyo Mitsubishi UFG Ltd | " |
| 36 | The Export- Import Bank of China | " |
| 37 | The Royal Bank of Scotland PLC (RBC) | " |
| 38 | The Standard Bank of South Africa Ltd | " |
| 39 | UBS AG H.O | " |
| 40 | Uni Credito SPA, Milano | " |

*6.1.2 የcorrespondent ሂሳብ በሌለባቸው ባንኮች (Banks having SWIFT Bilateral Key with CBE) በኩል*

የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የ correspondent ሂሳብ ከከፈተባቸው 40 ታላላቅ ባንኮች በተጨማሪ የ correspondent ሂሳብ ካልከፈተባቸው 384 ባንኮች ጋር የ SWIFT ግንኙነት አለው፡፡ እነዚህ ባንኮች በብዙ ሃገራት ቅንጫፎች ያሏቸው በመሆኑ የቦንድ ግዢ ለመፈፀም የሚፈልግ ማንኛውም ግለሰብ ወደ እነዚህ ቅንጫፎች በመቅረብ ክፍያውን በቀላሉ ወደ ኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ማስተላለፍ ይችላል፡፡ የባንኮቹ ዝርዝር ከዚህ ሰነድ ጀርባ አባሪ (Annex) የተደረገ ሲሆን በተጨማሪም ከየኤምባሲዎቹና የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ድረ-ገፅ (www.combanketh.com) ማግኘት ይቻላል፡፡

የCorrespondent ሂሳብ የሌለባቸውን ባንኮች ተጠቅሞ ገዢው በዶላር ወይም ዩሮ ወይም ፓውንድ ስተርሊንግ 1000 እና በላይ ክፍያ የሚፈፅም ከሆነ የመላኪያ ወጪው ሙሉ በሙሉ በመንግስት የሚሸፈንለት ይሆናል፡፡

ለ ቦንድ ገዢው ክፍያ ለመፈፀም በተ.ቁ.6.1 ንዑስ ተ.ቁ. 6.1.1 ሥር የተዘረዘሩት ቅደም ተከተሎች (steps) መከተል ይችላል፡፡

## 6.2 የክፍያውን ገንዘብ በኤምባሲ በኩል ወደ ኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ማስተላለፍ

ማንኛውም ሰው በአቅራቢያው በሚገኝ ኤምባሲ ወይም ቆንሲላ ወይም ልዩ መልዕክተኛ ጽ/ቤት በመቅረብ የቦንድ ግዢ መፈፀም ይችላል፡፡ ኤምባሲ ተሄዶ ለሚፈፀም ማንኛውም የቦንድ ግዢ የመላኪያ ክፍያ አይጠየቅም፡፡

Step 1:- ገዢው ፓስፖርት ወይም የኮሚኒቲ መታወቂያ ወይም ተወላጅነት ማረጋገጫ መታወቂያ ይዞ ወደ ›?Uvc= በመቅረብ የማመልከቻ ቅፅ ይሞላል፡፡

Step 2:- ገዢው ክፍያውን ለኤምባሲ ሲፈፅም ወዲያውኑ የቦንድ ኩፖን ከኤምባሲው ያገኛል፡፡

## 6.3 የክፍያውን ገንዘብ በገንዘብ አስተላላፊ ኤጀንት /Money transfer Agent/ በኩል ወደ ኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ማስተላለፍ

